**በለንደን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ**

# በታላቋ ብሪታንያ ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን

በግል በመመዝገብ ሆነ በመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ በመደራጀት በትግራይ ፣አማራ ፣ ኦሮሚያ ፣ ሶማሌ ፣ ቤንሻንጉል ፣ ጋምቤላ ፣ ደቡብ ፣ ሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና ድሬዳዋ አስተዳደር ቤት ለመገንባት ፍላጐት ላላችሁ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን የዳያስፖራ ቤቶች ልማት ፕሮግራም ምዝገባ በተመለከተ መታወቅ የሚገባቸው መረጃዎች ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## ለኢትዮጵያውያን የምዝገባ መስፈርቶች

1. የፀና ፓስፖርት ቅጂ
2. የሚኖሩበት አገር የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አደረጃጀች ባሉባቸው አገሮች የኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ካርድ ወይም በሚሲዮኑ ተረጋግጦ የሚሰጥ ማስረጃ፣
3. ያገባ ከሆነ/ች ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን፣
4. ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ
5. ለምዝገባው የተዘጋጁ ቅጾችን ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣
6. ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትደር ጓደኛ ስም በመረጡበት ክልል/ከተማ አስተዳደር ውስጥ የመኖሪያ ቤት ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሦስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣
7. የቤቱን ግንባታ ወጪ 50 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል በውጭ ምንዛሪ (በዶላር፣ በዩሮ ፣ በፓውንድ) የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚዮስቀምጥና መሬት ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ሲሰጥ ቀሪውን 50% ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመወሰድ ዝግጁ የሚሆን፣
8. የቤቱን ግንባታ ወጪ 50 በውጭ ምንዛሪ አገር ውስጥ በባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ፣

## ለትውልደ-ኢትዮጵያውያን የምዝገባ መስፈርቶች

1. የፀና ፓስፖርት ቅጂ
2. የፀና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቅያ ካርድ ቅጂ፣
3. ያገባ ከሆነ/ች ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን፣
4. ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ
5. ለምዝገባው የተዘጋጁ ቅጾችን ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣
6. ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትደር ጓደኛ ስም በመረጡበት ክልል/ከተማ አስተዳደር ውስጥ የመኖሪያ ቤት ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሦስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣
7. የቤቱን ግንባታ ወጪ 50 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል በውጭ ምንዛሪ (በዶላር፣ በዩሮ ፣ በፓውንድ) የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚዮስቀምጥና መሬት ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ሲሰጥ ቀሪውን 50% ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመወሰድ ዝግጁ የሚሆን፣
8. የቤቱን ግንባታ ወጪ 50 በውጭ ምንዛሪ አገር ውስጥ በባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ፣

## የባንክ ሂሳብ አከፋፈት

1. በቤት ልማት ፕሮግራሙ ለመሳተፍ የሚፈልጉ የዳያስፖራ አባላት በሥማቸው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለፕሮግራሙ በተዘጋጀው አካውንት ፎርም ይሞላሉ፡፡
2. ሚስዮኑ በዳያስፖራ አባላት የተሞላውን የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ ምዝገባ ፎረሞች ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስተላልፋል፡፡
3. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በደረሰው መረጃ መሠረት ለዳያስፖራ አባላቱ የባንክ ሂሳብ በመክፈት ለሚስዮኑ ያሳውቃል፡፡
4. ሚስዮኑ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የደረሰውን የአካውንት መረጃ ለተመዝጋቢ ዳያስፖራ አባላትና ማህበራት ያሳውቃል፡፡
5. የዳየስፖራ አባላቱ በሚስዮኑ በኩል የደረሰቻወን የግል የባንክ አካውንት በመጠቀም መርጠው ለተመዘገቡትና ለተደራጁበት የመኖረያ ቤት የግንባታ ወጪ የቅድሚያውን 50 % በውጭ ምንዛሪ ያስተላልፋሉ ፡፡ ደረሰኝ ቅጂ ይይዛሉ፡፡

# በለንደን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ

## በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው የሚመዘገቡት የዳያስፖራ አባላት

1. በመጀመሪያ መደራጀት የሚፈልጉበትን ክልል/ከተማ አስተዳደር ይመርጣሉ፣
2. በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የአደረጃጀት መመሪያ መሠረት የአባላቱን ቁጥር ይወስናሉ፡፡ የአደረጃጀት ሞዴል መተዳደርያ ደንብ እና  መመሪያው ከኤምባሲው ይሰጣቸዋል፡፡
3. የመስራች ስብሰባ ለመሥራት በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የማህበር መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የማህበራቸውን መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅተው ያፀድቃሉ፣ ማህበሩን ይመሠረታሉ፡፡
4. በምስረታው ስብሰባው የሥራ አመራር ም/ቤት የሥራ አመራር ኮሚቴ፣ የቁጥጥር ኮሚቴ፣ የቴክኒክና የማህበራዊ ኮሚቴ እና እንደ አስስፈላጊነቱ ሌሎችንም ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ፡፡ የአመራር አባላትም ምርጫ ያደርጋሉ፡፡
5. ሁሉም የማህበሩ አባላት የመስራች ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ፣ የመተዳደሪያ ደንብ እና የመስራች አባላት ዝርዝር ቅጽ ላይ ፊርማቸውን ያኖራሉ፣
6. ማህበሩ በህጋዊ መንገድ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር መመዝገብ የሚችለው ሁሉም የማህበሩ አባላት የተገመተውን የግንባታ ወጪ 50 በመቶ በውጭ ምንዛሪ (በዶላር፣ በዩሮና በፓውንድ) በምዝገባ ወቅት መክፈል ሲችሉ እና መሬት ተዘጋጅቶ ማህበሩ ሲረከብ የቀሪውን 50 በመቶ ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመውሰድ ዝግጁ ሲሆኑ ብቻ ይሆናል፡፡
7. ማህበሩ የእያንዳንዳን አባል የተሟላ ሰነድና ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ ያደረጉበትን ደረሰኝ በማያያዝ በሚሲዮኑ ወይም ሚሲዮኑ በሚያመቻቸው የምዝገባ ቦታ ወይም **በኢትዮጵያ ህዳሴ ም/ቤቶች** ዘንድ በአካል ተገኝተው ምዝገባ ያካሂዳሉ፡፡
8. የኢትዮጵያ ህዳሴ ም/ቤቶች መስፈርቱን አሟልቶ የተደራጁ ማህበራትን ሰነድ ከተቻለ በአካል ካልሆነም በተመዘገበ ፖስታ ለሚሲዮኑ በአድራሻ ይልካሉ፡፡ ስለመድረሱም መተማመኛ ከሚሲዮኑ ይረከባል፡፡ ለማህበሩ የመተማመኛውን ኮፖ ይሰጣሉ፡፡
9. ሚሲዮኑ የተደራጁ ማህበራት ሙሉ መረጃ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በፓውች ይልካል፡፡ ዳይሬክቶሬት ጄኔራሉም የማህበራቱ ሰነድ ስለመድረሱ ለሚሲዮኑ ያሳውቃል፡፡
10. በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የማህበራቱን ሙሉ መረጃ ከሸኚ ደብዳቤ ጋር ለመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር እንዲያደርሱ ለማህበራቱ ተወካዮች ስለመቀበላቸው አስፈርሞ ያስረክባል፡፡
11. ክልሉ/ከተማ አስተዳድሩ ለማህበራቱ እውቅና መስጠቱን፣ መሬትና የግንባታ ፈቃድ መዘጋጀቱን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራልና ለማህበራቱ ተወካዮች ያሳውቃል፡፡
12. በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ለመኖሪያ ህብረት ሥራ ማህበሩ እውቅና መስጠቱን እንዲሁም መገኘቱን፣ ለማህበሩ መሬትና የግንባታ ፈቃድ መዘጋጀቱን ለሚሲዮኑ ይገልጻል፡፡
13. ሚሲዮኑ ይህንኑ ለማህበራቱ ያሳውቃል፡፡
14. ማህበሩ ሁሉም አባላት ቀሪውን 50 በመቶ ወደ ማህበራቱ ዝግ አካውንት ማስተላለፋቸውን በማረጋገጥ መረጃውን ለሚሲዮኖች ያሳውቃል፡፡
15. ሚሲዮኑ ቀሪውን 50 ክፍያ ፈፅመው ያጠናቀቁ ማህበራት መረጃ ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ያስተላልፋል፡፡
16. የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ጄኔራል ቀሪውን 50 ክፍያ ፈፅመው ያጠናቀቁ ማህበራት መረጃ ለማህበሩ ተወካያችና ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያሳውቃል፡፡
17. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የማህበሩ አካላት ለቤቱ ግንባታ የሚያስፈልገውን 100%  ወጪ በውጭ ምንዛሪ ማስገባታቸውን፣ ቀጥሎም በብር ወደ ማህበሩ አካውንት መተላለፉን በማረጋገጥ ለክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ የማህበራት አደራጅ አካልና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳ/ጄኔራል ያረጋግጣል፡፡
18. የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ አደራጅ አካል ማህበራቱ የግንባታውን 100 ከፍለው ማጠናቀቃቸውን ከኢትያጵያ ንግድ ባንክ ማረጋገጫ ሲደርሰው ለማህበራቱ መሬትና የግንታታ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ይለካል፣ ለማህበራቱ ተወካዮች በግልባጭ ያሳውቃል፡፡

# በለንደን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ

## በግል የመኖሪያ ቤት ተመዝጋቢዎች

1. በግል የሚመዘጉ የዳያስፖራ አባላት የሚፈልጉትን ክልል/ከተማ አስተዳደር በመምረጥ የሚፈልጉትን የቤት ዓይነት ይመርጣሉ፣
2. ቤቱን ለመገንባት ከሚያስፈለገው ወጪ ደረጃ የሚጠበቅባቸውን 50 በመቶ ክፍያ በምዝገባ ወቅት ከሚኖሩበት ሀገር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ሂሳብ በመክፈት ገንዘብ በውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ቤት በመላክ ወደ ተከፈተው አካውንት ያስተላለፉበትን ደረሰኝ ቅጂ ተሞልቶ ከተፈረመው የመመዝገቢያ ቅጽ ጋር በማያያዝ ለሚሲዮኑ ያቀርባሉ፡፡
3. በግል የተመዘገቡ የዳያስፖራ አባላት በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የማህበራት አደረጃጀት መመሪያ መሠረት ዝቅተኛውን ቁጥር ሲያሟሉ ሚሲዮኑ በማህበር እንዲደራጁ በማድረግ መረጃውን ወደ ዋናው መ/ቤት የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይላካል፡፡
4. የግል ተመዝጋቢዎችን በተመዘገቡበት ሚሲዮን በሚኖሩበት አገር በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የአደረጃጀት መመሪያ መሠረት በማህበር ዝቅተኛው ቁጥር የማይሞሉ ከሆነ ከሚሲዮኑ መረጃቸው በሸኚ ደብዳቤ ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬቶሬት ጄኔራል ይላካል፡፡
5. በግል የመጡ መረጃዎችን ወደ መረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር በዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል አማካኝነት ይላካል፡፡
6. ክልሉ/ከተማ አስተዳደር በተመሳሳይ መልኩ ከሌላ ሚሲዮን ዝቅተኛውን የማህበር አባላት ቁጥር ሳይሞላ ከተላኩ ጋር በማህበር እንዲደራጁ በማድረግ መረጃውን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለተወካየቻቸው ያሳውቃል፡፡

## ትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

| ተ.ቁ | የቤት ዓይነት | ስፋት | ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | ባለሁለት መኝታ ክፍል አፓርታማ ( G+ 2 እና በላይ) | 74 ካሬ ሜትር | 424,390 ብር |
| 2 | ባለ ሦስት መኝታ ክፍል አፓርታማ ( G+ 2 እና በላይ) | 100 ካሬ ሜትር | 573,500 ብር |
| 3 | ባለ አራት መኝታ ክፍል አፓርታማ( G+ 2 እና በላይ) | 136 ካሬ ሜትር | 779,960 ብር |

## አማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

| ተ.ቁ | የቤት ዓይነት | ስፋት | ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | ባለሁለት መኝታ ክፍል አፓርታማ | 74 ካሬ ሜትር | 424,390 ብር |
| 2 | ባለ ሦስት መኝታ ክፍል አፓርታማ | 100 ካሬ ሜትር | 573,500 ብር |
| 3 | ባለ አራት መኝታ ክፍል አፓርታማ | 136 ካሬ ሜትር | 779,960 ብር |
| 4 | ታውን ሃውስ (G+2) ባለ ሦስት መኝታ | 114 ካሬ ሜትር | 693,120 ብር |
| 5 | ታውን ሃውስ (G+2) ባለ ሦስት መኝታ | 150 ካሬ ሜትር | 912,000 ብር |

## ኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

| ተ.ቁ | የቤት ዓይነት | ስፋት | ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | ባለሁለት መኝታ ክፍል አፓርታማ | 80 ካሬ ሜትር | 400,000 ብር |
| 2 | ባለ ሦስት መኝታ ክፍል አፓርታማ | 100 ካሬ ሜትር | 550,000 ብር |
| 3 | ባለ አራት መኝታ ክፍል አፓርታማ | 110 ካሬ ሜትር | 700,000 ብር |
| 4 | G+1 እና G+2 ታውን ሃውስ | 80 ካሬ ሜትር | 800,000 ብር |

# በለንደን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ

## ሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

| ተ.ቁ | የቤት ዓይነት | ስፋት | ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | ባለሁለት መኝታ ክፍል አፓርታማ | 74 ካሬ ሜትር | 424,390 ብር |
| 2 | ባለ ሦስት መኝታ ክፍል አፓርታማ | 100 ካሬ ሜትር | 573,500 ብር |
| 3 | ባለ አራት መኝታ ክፍል አፓርታማ | 136 ካሬ ሜትር | 779,960 ብር |
| 4 | ታውን ሃውስ (G+2) ባለ ሦስት መኝታ ክፍል | 114 ካሬ ሜትር | 693,120 ብር |
| 5 | ታውን ሃውስ (G+2) ባለ አራት መኝታ ክፍል | 150 ካሬ ሜትር | 912,000 ብር |

## ጋምቤላ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

| ተ.ቁ | የቤት ዓይነት | ስፋት | ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | ባለሁለት መኝታ ክፍል አፓርታማ | 74 ካሬ ሜትር | 424,390 ብር |
| 2 | ባለ ሦስት መኝታ ክፍል አፓርታማ | 114 ካሬ ሜትር | 693,120 ብር |
| 3 | ባለ አራት መኝታ ክፍል አፓርታማ | 150 ካሬ ሜትር | 912,000 ብር |
| 4 | ታውን ሃውስ (G+2) ባለ ሦስት መኝታ ክፍል | 114 ካሬ ሜትር | 693,120 ብር |
| 5 | ታውን ሃውስ (G+2) ባለ አራት መኝታ ክፍል | 150 ካሬ ሜትር | 912,000 ብር |

## ደቡብ ብሄር ብሄረሰብ እና ህዝቦች ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

| ተ.ቁ | የከተሞች ደረጃ | የግንባታ ዓይነት | የመኝታ ቤት ብዛት | ስፋት | ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **መሪ ከተማ ሀዋሣ** | (G+4) አፓርትመንት | ባለ 2 መኝታ ክፍል | 80ካ/ሜ | 770,720.98 |
| | | | ባለ 3 መኝታ ክፍል | 95ካ/ሜ | 824,911.15 |
| | | | ባለ 4 መኝታ ክፍል | 110ካ/ሜ | 876,049.35 |
| 2 | **ከፍተኛ የከተማ አስተዳደሮች**<br>አርባ ምንጭ፣ወላይታ ፣ ዲላ ፣ ሆሳእና | (G+3) አፓርትመንት | ባለ 2 መኝታ ክፍል | 85ካ/ሜ | 840,208.61 |
| | | | ባለ 3 መኝታ ክፍል | 100ካ/ሜ | 926,571.12 |
| | | | ባለ 4 መኝታ ክፍል | 115 ካ/ሜ | 959,128.58 |
| 3 | **መካከለኛ የከተማ አስተዳደር ከተሞች**<br>ወልቂጤ፣ ቡታጅራ፣ ሚዛን አማን፣ቴፒ፣ይርጋለም | G+2 ታውን ሃውስ | ባለ 2 መኝታ ክፍል | 90ካ/ሜ | 840,076,79 |
| | | | ባለ 3 መኝታ ክፍል | 105 ካ/ሜ | 912,422.86 |
| | | | ባለ 4 መኝታ ክፍል | 120 ካ/ሜ | 956,890.70 |
| 4 | **ታዳጊ የከተማ አስተዳደር ከተሞችና ማዘጋጃ ቤቶች**<br>ወራቤ፣ሀላባ፣ ይርጋጨፌ አለታ ወንዶ፣ ቦዲቲ ፣<br>አረካ ፣ዱራሜ ቦንጋ ፣ ሳውላ ፣ጂንካና ታርጫ | G+0 ታውን ሃውስ | ባለ 2 መኝታ ክፍል | 80 ካ/ሜ | 204,544.70 |
| | | | ባለ 3 መኝታ ክፍል | 90ካ/ሜ | 242,378.78 |
| | | | ባለ 4 መኝታ ክፍል | 100ካ/ሜ | 278,<br>736.00 |

# በለንደን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ

## ሐረሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

| ተ.ቁ | የቤት ዓይነት | ስፋት | ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | ባለሁለት መኝታ ክፍል አፓርታማ ( G+ 4 እና በላይ) | 74 ካሬ ሜትር | 424,390 ብር |
| 2 | ባለ ሦስት መኝታ ክፍል አፓርታማ ( G+ 4 እና በላይ) | 100 ካሬ ሜትር | 573,500 ብር |
| 3 | ባለ አራት መኝታ ክፍል አፓርታማ ( G+ 4 እና በላይ) | 136 ካሬ ሜትር | 779,960 ብር |
| 4 | ታውን ሃውስ (G+2) ባለ ሦስት መኝታ ክፍል | 114 ካሬ ሜትር | 693,120 ብር |
| 5 | ታውን ሃውስ (G+2) ባለ አራት መኝታ ክፍል | 150 ካሬ ሜትር | 912,000 ብር |
| 6 | ባለ አራት  መኝታ ክፍል G+1 ታውን ሃውስ የክልሉ ባህላዊ ኪነህንፃ ጥበብ ያማከለ | 129.63 ካሬ ሜትር | 788,150 ብር |
| 7 | ባለ ስድስት  መኝታ ክፍል G+2 ታውን ሃውስ የክልሉ ባህላዊ ኪነህንፃ ጥበብ ያማከለ | 181.18 ካሬ ሜትር | 1,101,574ብር |
| 8 | ባለ 7 መኝታ ክፍል ታውን ሃውስ የክልሉ ባህላዊ ኪነህንፃ ጥበብ ያማከለ G+1 | 247.55ካሬ ሜትር | 1,505,104ብር |

## ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር

| ተ.ቁ | የቤት ዓይነት | ስፋት | ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | ታውን ሃውስ ባለሁለት መኝታ ክፍል | 128  ካሬ ሜትር | 582, 400 ብር |
| 2 | ታውን ሃውስ ባለ ሦስት መኝታ ክፍል | 160  ካሬ ሜትር | 728, 000  ብር |
| 3 | ታውን ሃውስ  ባለ አራት መኝታ ክፍል | 200 ካሬ ሜትር | 910, 000 ብር |

## ቤንሻንጉል ጉሙዝ  ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

| ተ.ቁ | የቤት ዓይነት | ስፋት | ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | ባለ ሁለት መኝታ ክፍል አፓርታማ ( G+ 2 እና በላይ) | 74 ካሬ ሜትር | 424,390 ብር |
| 2 | ባለ ሦስት መኝታ ክፍል አፓርታማ ( G+ 2 እና በላይ) | 100 ካሬ ሜትር | 573,500 ብር |
| 3 | ባለ አራት መኝታ ክፍል አፓርታማ( G+ 2 እና በላይ) | 136 ካሬ ሜትር | 779,960 ብር |
| 4 | ቪላ G+1 ባለ ሦስት መኝታ | 114 ካሬ ሜትር | 693,120 ብር |
| 5 | ቪላ G+1   ባለ አራት መኝታ | 150 ካሬ ሜትር | 912,000 ብር |